## ክፍል 5 አድልዎ ፣ማሕበረሰባዊ ጥቃትና የሰዎች ዝውውር ንግድ

ሕጉ ማንኛውንም በዘር ፣ በቀለም ፣ በጾታ፣ በቋንቋ፣ በብሔር፣ በፖለቲካና ሌላ አመለካከት ወይም በሕብረተሰቡ ውስጥ ባለው ቦታ የሚደረግ አድልዎን ይከለክላል። ይሁን እንጂ መንግሥት እነዚህን ገደቦች በተግባር አላስፈፀመም ነበር።

ሴቶች፣

የቤት ውስጥ ጥቃት ፣ በባሎች የሚፈፀሙ ድብደባዎችንና የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን ጨምሮ ፣ ሰፊ ማህበረሰባዊ ችግሮች ነበሩ። ሐምሌ 2005 በተደረገው በዓለም ባንክ ጥናት ላይ 88 በመቶ የሚሆኑ የገጠር ሴቶችና 69 በመቶ የሚሆኑ የከተማ ሴቶች ባሎቻቸው ሊመቷቸው መብት አላቸው ብለው ያምኑ እንደነበር ደምድሟል።

ምንም እንኳን ሴቶች ለፖሊስና ለፍርድ ቤት ማመልከት ቢችሉም የማህበረሰቡ ደንቦችና ውሱን የሆነው መሠረተ ልማት ብዙ ሴቶች፤ በተለይም በገጠሩ አካባቢ፤ ወደ ሕግ እንዳይሄዱ አግደዋቸዋል። መንግሥት በተወሰነ ደረጃ አጥፊዎችን ወደ ሕግ አቅርቧል።

በጥቅምት 2005 መንግሥት የሴቶች ጉዳይ ቢሮን ወደ ሴቶች ጉዳይ ሚኒስቴር ከፍ አድርጎት ነበር ። ይህ ሚኒስቴር ራሱን የቻለና ተጨማሪ ሠራተኞች ያሉት ነበር ። ሌሎች ሁሉ አስፈላጊ ቢሮዎችን በ2005 ተከፍተው ነበር ። እነሱም በኢትዮጵያ ሰብዓዊ መብቶች ኮሚሽን ውስጥ በምክትል ምኒስትር ማዕረግ በተሾሙ የሴቶችና የሕፃናት ኮሚሽነር የሚመራውና በእንባ ጠባቂው ቢሮ የሴቶችና የህፃናት ዕንባ ጠባቂ ቢሮ ነበሩ። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ አስገድዶ መድፈርን ወንጀል ቢያደርገውም በትዳር ውስጥ ስለሚፈፀመው አስገድዶ መድፈር ግን በግልፅ ያስቀመጠው ነገር የለም ። መንግሥት ይህንን አንቀፅ ሙሉ ለሙሉ ተፈፃሚ እንዲሆን አላደረገም ነበር ። ለዚህም ምክንያቶቹ

የሕዝቡ በተለይም የሴቶች አለማወቅና የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችና ገንዘብ አለመኖር ነበሩ።

የማህበረሰቡ ደምቦች በተለይ በገጠሩ አካባቢ የችግሩ ቁልፍ መንስኤዎች ሆነው ቆይተዋል። የማሕበረሰቡ ደምቦች የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን በመከታተሉና ለሕግ በማቅረቡ ሂደት ላይ እንቅፋት ሆነው ነበር ። ከዚህም በተጨማሪ ብዙ ሴቶች በሕግ ስለተሰጣቸው መብት አለማወቃቸው ሪፖርት የማይደረጉ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች እንዲበዙ አድርጓል። ታዛቢዎች እንደገመቱት በአዲስ አበባ ብቻ መደ 1000 አካባቢ የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎች በየዓመቱ የፈፀማሉ ። ነገር ግን የፖሊስ መረጃ እንደሚያመለክተው በዓመት በግምት ወደ 400 ያህል ብቻ ነበር ሪፖርት የሚደረጉት ። ጋዜጦች በቋሚነት የአስገድዶ መድፈር ወንጀሎችን በተለይም በሕፃናት ላይ አደጋ ሲደርስ ሪፖርት ያደርጉ ነበር ። የተፈረደባቸውን አስገድዶ ደፋሪዎች ፍርድ ቤቶች ከ10 እስከ 15 ዓመት በሚደርስ እስራት በሕጉ በተቀመጠው መሠረት ቀጥተው ነበር ።

ምንም እንኳን ሕገ ወጥ ቢሆንም አማራን፤ ኦሮሚያንና ደቡብ ብሔር ብሔረሰቦችና ሕዝቦች ክልሎችን ጨምሮ፤ ባብዛኛው ያገሪቱ ክልሎች ጠለፋ አንዱ የጋብቻ መንገድ ሆኖ ቀጥሎ ነበር ። መንግሥትም ይህንን ተግባር ለመዋጋት ጥረት አድርጎ ነበር ። ያለፍላጎት የሚደረግ የግብረሥጋ ግንኙነት የአብዛኛው የጥልፊያ ግብቻዎች መገለጫ ሲሆን ብዙ ጊዜም በጠለፋ ወቅት ሴቶች አካላዊ ጉዳት ይደርስባቸዋል። ጠለፋዎች በቤተሰቦች፤ በማህበረሰቦችና በጎሣዎች መሃከል ግጭቶችን አስከትለዋል ። በጥልፊያ በሚፈፀም ጋብቻ ጠላፊው ተጠላፊዋ ልታገባው ከተስማማች አይቀጣም፤ ባለስልጣናት ጋብቻውን ካልሰረዙት በቀር። ጠላፊው በጥፋተኝነት

ከተፈረደበት በኋላ እንኳን ባለስልጣናት ተጠቂዋ ልታገባው ከፈቀደች ፍርዱን አያስፈጽሙም ነበር። ያለእድሜ ጋብቻም፣ በለተይ በአማራና ትግራይ ክልሎች፣ ሌላው ችግር ነበር። በነዚህ ክልሎች ሴት ልጆች 7 ዓመት ሲሞላቸው ለጋብቻ ይገደዳሉ፣ ምንም እንኳን ሕጉ የጋብቻ እድሜ 18 ዓመት ነው ቢልም። ያለእድሜ ጋብቻን ጨምሮ በሴቶችና ልጃገረዶች ላይ ስለሚደርሱ ጥቃቶች የሕብረተሰቡ ግንዛቤ እያደገ እንደነበር የሚያሳዩ ምልክቶች ነበሩ።

አብዛኛው የሀገሪቱ ልጃገረዶችና ሴቶች ግርዛት ተፈጽሞባቸዋል። ልጃገረዶች ገና ሰባት ቀን ሲሆናቸው የሚገረዙ ሲሆን በኮረዳነታቸው ደግሞ ባሰቃቂ ሁኔታ ብልታቸውን ይሰፋሉ። በ2005ቱ የጤና ጥበቃ ሚኒስቴር የሕዝብ ብዛትና ጤና ዳሰሳ መሠረት በሴቶች ላይ የሚደረገው ግርዛት ከ80 በመቶ ወደ 74 በመቶ እንዲሁም ሴቶች ለግርዛት የነበራቸው ድጋፍ ከ60 በመቶ ወደ 29 በመቶ ቀንሷል። የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉ ማንንም ሴት መግረዝ ከ3 ወር ባላነሰ እስራት ወይም ከ500 ብር ባላነሰ ቅጣት እንደሚያስቀጣ ይደነግጋል። በተመሳሳይም የሴት ልጅን ብልት መስፋት ከ5 እስከ 10 ዓመት በሚደርስ እስራት ያስቀጣል። ይሁን እንጂ ግርዛትን በተመለከተ ምንም አይነት ክስ ፍርድ ቤት አልቀረበም ነበር።

መንግስት ግርዛትን ለማጥፋት የተወሰኑ እርምጃዎችን ወስዷል፣ ይሄ ተግባር እንዳይቀጥልም በሕዝብ ትምህርት ቤቶችና በመገናኛ ብዙሃን በዘመቻ አስተምሯል።

በለጋ ዕድሜ የሚከሰት እርግዝና፤ የእናቲቱ ከባድ የተመጣጠነ ምግብ እጦትና በወሊድ ጊዜ ተገቢውን እንክብካቤ የሚያደርጉ ባለሞያዎች እጦት ለፌስቱላና ለዘላቂ የሽንትና የሰገራ መቆጣጠር ችግር ይዳርጋሉ ። በግምት ወደ 8,700 የሚጠጉ ሴቶች በየዓመቱ በፊስቱላ ችግር ይሰቃያሉ ። ከዚህም በላይ 27,000 ሕክምና ያላገኙ የፊስቱላ ታማሚ ሴቶች በገጠር እንደሚኖሩ ታውቋል ። ለፊስቱላ በሽታ ሕክምና የሚገኘው አዲስ አበባ ባለው ብቸኛው የፊስቱላ ሆስፒታል ነበር ። በዚሁ ሆስፒታል በየአመቱ ከ1000 በላይ የፊስቱላ ቀዶ ህክምናዎች ይደረጋሉ ። ለእያንዳንዱ ውጤታማ ቀዶ ጥገና አሥር ሌሎች ወጣት ልጃገረዶች ሊታከሙ ቢገባም ግን ሕክምና አያገኙም ነበር ። በወሊድ ጊዜ የሚከሰት ሞት መጠን በጣም ከፍተኛ ነበር ። ይህም በከፊል ለነፍሰጡር ሴቶች የሚከለከሉ ምግቦች በመኖራቸው፤ በድህነት፤ ካለ ዕድሜ ጋብቻና ከግርዘት በተለይም የሴትን ብልት ከመስፋት ጋር የተያያዙ የወሊድ ችግሮች በሚያስከትሉት ችግር ነበር የሚከሰተው ።

እድሜያቸው ከ18 በላይ ለሆኑ ሰዎች ሴትኛ አዳሪነት ሕጋዊ የነበረ ሲሆን የሴተኛ አዳሪ ድለላና በሴተኛ አዳሪነት ከሚገኝ ገቢ ትርፍ ማካበት በሕግ የተከለከሉ ነበሩ። በሴተኛ አዳሪነት የተሰማሩ ሰዎች በተደጋጋሚ ድህነት ወደዚህ ዓይነት ሥራ እንደስገባቸው ሪፖርት ያደርጉ ነበር ።

የህግ ባለሞያ ቤቶች ማህበርና አለማቀፍ የስደተኞች ድርጅት ( አይ ኦ ኤም )ብዙ ወደ መካከለኛው ምሥራቅ በኢንዱስትሪዎችና በግለሰብ ቤቶች ለመሥራት የሚጓዙ ሴቶች እንግልት እንደሚደርስባቸው ሪፖርት አድርገዋል። (ክፍል 5፤ ሕገወጥ ዝውውርን ይመልከቱ)

የፆታ ወከባ ተስፋፍቶ ነበር ። የወንጀለኛ መቅጫው ከ18 እስከ 24 ወራት የሚደርስ የእስር ቅጣት ቢደነግግም የፆታ ወከባን የተመለከቱ ሕጎች ተፈፃሚ አልነበሩም ። ምንም እንኳን ሕጉ ሁሉም ሰው እኩል ነው ቢልም መንግሥት ይሄን ሕግ በአግባቡ አላስፈፀመም ነበር። ሕጉ የወንድና ሴት ልጆች ሕጋዊ የጋብቻ ዕድሜ 18 እንደሆነ አስቀምጧል ፤ የፍትሐብሔር ሕጉ ከባህላዊ ሃይማኖታዊ ሕጎች በላይ እንዲሆን አድርጓል፤ በትንሹ ለ5 ዓመታት አብረው የኖሩ ያልተጋቡ ግለሰቦች እኩል ንብረት እንዲካፈሉና የቤተሰብ ሽምግልና ጉባዔዎች እንዲቀሩ አድርጓል፤ ፍርድ ቤቶች በፍቺና መለያየት ወቅት የልጆችን ወይም አቅም የሌለውን የቤተሰብ አባል ሁኔታ ግምት ውስጥ እንዲያስገቡ አዟል፤ በሴቶች ላይም ከፍቺ በኋላ ወይም ባሎቻቸው ከሞቱ በኋላ ድጋሚ